# ለ20ኛ ጊዜ የሚከበረው የብሄር ብሄረሰቦች በዓል አከባባር

ለ20ኛጊዜ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን "ዲሞክራስያዊ መግባባት ለህብረ ብሄራዊ አንድነት" በሚል መልዕክት፤ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሆሳና ከተማ ህዳር 29 ቀን 2018 ዓ.ም ይከበራል፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል በየዓመቱ የሚከበረ የህዝቦች ትስስርን በማጠናከር እና በማጎልበት ህብረ-ብሄራዊ አንድነትን በጠንካራ መሰረት ላይ እንዲገነባ ከፍተኛ ፋይዳ ያለዉ በመሆኑ ክብረ በዓሉ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህላቸውንና ማንነታቸውን ለማስተዋወቅ ዕድል ይፈጥራል፡፡ በ1987ዓ.ም የፀደቀው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የብሔር ብሔረሰቦችን መብት የሚያረጋግጥ፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰንና መብትን የሚጐናፅፍ በመሆኑና የባሕላዊ እሴቶቻችን ለሚዲያ ተደራሽ የምናደርግበት ነው፡፡ ይህ በዓል የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች በታሪክ ለሀገሪቱ የበለፀገ የባህል ቅርስ አስተዋፅዖ ያበረከቱትን አንድነት አስፈላጊ መሆኑን አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ለዘመናት ተግባብተውና ተስማምተው የኖሩ የሕዝቦቿን የዳበሩ ባህሎች፣ ቋንቋዎችና ትውፊቶችን ይበልጥ እንዲደምቁ የሚያደርግ ሲሆን፣ ሀገራዊ መግባባትን በእጅጉ ያጠናክራል፡፡ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህላቸውን ለማክበር እና የማይናወጥ ብሄራዊ አንድነት እንዲጎለብት ከማድረጉም ባሻገር በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል አብሮነትን ለማጠናከር ወሳኝ ሚና አለው፡፡

ዲሞክራሲያ መግባባት ለህብረ ብሔራዊ አንድነት የሚለዉ መሪ ቃል በኢትዮጵያ ማኅበራዊ ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚኖዊ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ እዉነታዎችን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ሲሆን በተለይ በኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል የጋራ መግባባት ከመፍጠሩም ባሻገር የተረጋጋ እና የበለጸገ የኢኮኖሚ እድገት እንዲረጋገጥ ከፍተኛ ሚና ያለው ሲሆን መንግስት የዘንድሮ የብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በዓል በማእከላዊ ኢትዩጱያ በሆሳና ከተማ እንዲከበር ማዘጋጀቱ ክልላዊ ብዝሃነትን እና አካታችነትን ለማስተዋወቅ ፋይዳ ያለው በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝቦች እንደመገኛና የሀገሪቱን የመድብለ-ባህላዊ መልክዓ ምድር ማሳያ መሆኗን በዓሉ የአንድነት፣ የሰላም፣ የመቻቻል እንዲሁም የሕብረ-ብሔራዊነት ቀለም መገለጫ ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያውያን የብዝሃ ባህል፣ ታሪክ፣ እሴትና የተፈጥሮ መስህብ ባለቤት መሆናቸውን ለዓለም የሚያስተዋውቁበት ልዩ ባዓል ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓሉ በአንድ መልከ የኢትዮጵያ ህዝቦችን ብዝሀነት አጉልቶ የማሳየት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ብዝሀነቱን ለማስተናገድ የሚያስችል ሥርዓት እንደተገነባና ብዝሀነታችን የልዩነታችንና የጥንካሬያችን መገለጫ እንዲሆነ ለማስመስከር የሚያገለግል እሴት በመሆኑ ትልቅ ትርጉምና ፋይዳ ያለው ነው፡፡የብሔረሰቦች

ቀን በዓልን ማክበር  ህገመንግሥቱ የፀደቀበትን ቀን መዘከር ማለት ነው፡፡ ህገ መንግስቱን መዘከር ማለት ደግሞ  ህገ መንሥቱ ያስገኘውን  ጥቅሞችና ድሎች የበለጠ በመንከባከብ የተመዘገቡትንም የልማትና የመልካም አስተዳደር ውጤቶች በማስፋፋት የእርስ በርስ መተጋገዝ በማጠናከር የበለጠ  የምንግባበት በዓል ይሆናል ማለት ነው፡፡ ህዝቦች በዳሞክራሲና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ አንድነታቸውን የሚያጠናክሩበት፣ ለአገራችን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም በወንድማማችነትና በመቻቻል አብሮ የመኖር ባህላቸውን የሚያንፀባርቁበት የነፃነትና የድልቸው ቀን በመሆኑ በታሪካዊነቱ የተለየ ቦታ ይሰጠዋል፡፡

በአጠቃላይ በየአመቱ ህዳር 29 በምናከብረው የብሔረሰቦች በዓል ብሔር ብሔረሰቦች ተገናኝተው ማንነታቸውን የሚያሳውቁበት፣ ባህላዊ እሴቶቻቸውን አጉልተው የሚያሳዩበት፣ ህገ መንግሥታዊ መብታቸው መከበሩን የሚገልጹበትና በዚህ ታሪካዊ ቀን ጠንካራ ተሞክሮዎቻቸውን በማጎልበት በተለይም የብሔሮች ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን ግንኙነትና አንድነት በማጠናከር አብሮ የመኖር ባህላቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ ረገድ በዓሉ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡